# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 17 ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ



# ፍትህ ለተጎዱ ወገኖቻችን !

ፍትህ ሚዛናዊነቷን በምታጣበት ወቅት ጉልበተኛ በዳይ ራሱን ተበዳይ አድርጎ በማቅረብ ከፍርድ ማምለጥ ብቻ ሳይሆን ከተበዳይ ካሳ መቀበል ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የፍትህ መዛነፍ በኢትዮጵያችን የተለመደና ስንታገለው የቆየ ነው፡፡

ፍትህ እንዳይዛነፍ የፀጥታ እና የደህንነት ተቋማት በደል ፈፃሚዎችን ለፍርድ በማቅረብ የተበዳዮችን እንባ ማበስ ይጠበቅባቸዋል፤ የዳኝነት ሥርዓቱም በዳዮች ተገቢውን ቅጣት ማግኘታቸው እና ተበዳዮች ለደረሰባቸው በደል ተመጣጣኝ ካሳ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ፍትህ በሚረገጥባቸው ሥርዓቶች ግን የሚስተዋለው የተገለፀው ተቃራኒ ነው፡፡ የፀጥታና የፍትህ ተቋማት ከበዳዮች ጎን ቆመው ለበደል ሽፋን ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዴም ለበዳዮች ሽፋን ከመስጠት አልፈው በበዳዮች ፋንታ ተበዳዮችን ይቀጣሉ፡፡ በዚህ መንገድ ፍርድ ይዛባል፡፡ ፍትህ ሲጓደል ዜጎች በሀገራቸው መንግሥት እምነት ያጣሉ፤ ለመንግሥትና መንግሥታዊ ተቋማት ያላቸው ክብር በእጅጉ ይቀንሳል፡፡ የፍትህ መጓደል ማኅበራዊ ቅራኔን ያባብሳል፡፡

በአሁኑ ወቅት የፍትህ ተቋሞቻችን በለውጥ ሂደት ውስጥ ያሉ መሆኑ ይነገራል፡፡ እነዚህ ተቋማት በርግጥም በአዎንታዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ መሆን አለመሆናቸው የሚፈተኑበት አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በማናቸውም መንገድ ለቅራኔ ባልተዘጋጁ ዜጎች ላይ፤ እንኳንስ ለማጥቃት ለመከላከል እንኳን ዝግጅት ባላደረጉ ወገኖቻችን ላይ የተደራጀ የአንድ ወገን ጥቃት (One-sided violence) ተፈጽሟል፡፡ ዜጎች በመኖሪያ ቤታቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት በሚያከናውበት ወቅት ሊያጠፋቸው በመጣ ኃይል ሕይወታቸው ተነጥቋል፤ ብዙዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ በብዙ ድካም ያፈሩት ንብረት ወድሟል፡፡

የፀጥታ፣ የደህንነትና የፍትህ ተቋሞቻችን በአዎንታዊ ለውጥ ሂደት ውስጥ መሆናቸውን የሚረጋገጠው የፓለቲካና የኃይል ሚዛንን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለዚህ የተደራጀ ወንጀል በሚሰጡት ምላሽ ነው፡፡ ይህ የተቋማቱ መፈተኛ ወቅት ነው፡፡

በለውጥ ሂደት ውስጥ ያሉት የፍትህ ተቋሞቻችን ወገንተኝነታቸው ለፍትህ ብቻ እንዲሆን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አበክሮ ይጠይቃል፡፡ የህግና ፍትህ ተቋማት ይህንን እጅግ አደገኛ የሆነ ወንጀል የፈፀሙ እና ያስፈፀሙ፤ ወጣቱን በስሜት ገፋፍተው አደባባይ እንዲወጣ ያደረጉ፤ ዘር መርጦ የመግደልን ሀሳብ በወጣቶች አዕምሮ እንዲሰርጽ ያደረጉ ሁሉ በሕግ እንዲጠየቁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሥርዓቱ ይህንን ማድረግ ሲችል ነው በርግጥም በለውጥ ሂደት ውስጥ ያለ መሆኑ ማረጋገጥ የሚቻለው፡፡

ይህ ጉዳይ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ስሱ ጉዳይ እንደሆነ ኢዜማ ይገነዘባል፡፡ በስሱነት ሰበብ ግን ፍትህ እንዳይዛነፍ ኢዜማ አበክሮ ያሳስባል፡፡ በዚህ የለውጥ ወቅት የፍትህ ሚዛን እንዳይዛነፍ ማድረግ ለለውጡ ስኬት ወሳኝ እንደሆነ ኢዜማ ይገነዘባል፡፡ ከሁሉም በላይ በደል ፈፃሚዎች በቸልታ የሚታለፉበት፤ በደል የተፈፀመባቸው ወገኖች የሚቀጡበት ፍርደገምድል አሠራር እንዳይደገም ጥንቃቄ እንዲደረግ ኢዜማ ያሳስባል፡፡

በዚህ አጋጣሚም መንግሥት የሕዝብን ሰላም የሚያስጠብቁ ዘላቂ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ በተለይም የኢትዮጵያ ወጣቶች በሕጋዊ ማኅበራዊ ስብስቦች እንዲሰባሰቡ፣ በሀገራቸውና በመጪው ጊዜ ተስፋ እንዲኖራቸው ማድረግ ለነገ የማይተው የመንግሥት ኃላፊነት እንደሆነ ማስታወስ ይወዳል፡፡

# ኢዜማ በዴንቨርና በዳላስ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥቅምት 22 እና ጥቅምት 23 ቀን 2012 ዓ.ም በዴንቨር እና በዳላስ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የስብሰባዎቹ ዓላማዎች ኢዜማን ማስተዋወቅ፣ ብዥታዎችን ማጥራት፣ ደጋፊዎችን ማሰባሰብና መመልመል እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ መሆኑን ተጠሪው አስረድተዋል፡፡ በስብሰባዎቹም ላይ ሀገሪቷ አሁን ስላላችበት ሁኔታ፣ ከዚህ ቀደም በኢዜማ በኩል ስለተሠሩ ሥራዎች፣ ኢዜማ ወደፊት ምን ለመሥራት እንዳቀደ፣ ኢዜማ በውጪ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምን እንደሚጠብቅና በውጪ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያለው ፖሊስ ምን ይመስላል የሚሉ ነጥቦች በሕዝባዊ ስብሰባው ላይ መነሳታቸውን ተጠሪው ገልፀዋል፡፡ በሕዝባዊ ስብሰባው ላይ ከታዳሚያን ለተነሱት የተለያዩ ጥያቄዎችም ዓለም አቀፍ አባለት ተጠሪው ኢዮብ መሳፍንትና ምክትል መሪው አንዱዓለም አራጌ ምላሾቻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ኢዜማን በመወከል በአሜሪካን ሀገር የሥራ ጉብኝት እያካሄዱ የሚገኙት ምክትል መሪው አንዱዓለም አራጌና ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪው ኢዮብ መሳፍንት እስካሁን ድረስ በሲያትል፣ ሎስአንጀለስ፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሳንሆዜ፣ ላስ ቬጋስ፣ አትላንታ፣ ዴንቨር እና ዳላስ ከተሞች ከሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ተወያይተዋል፡፡ በቀጣይም ጥቅምት 30 ቀን 2012 ዓ.ም በቦስተን እንዲሁም ሕዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም በሚኒሶታ ከተማ ከሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር የሚወያዩ ይሆናል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)


ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ

## የኢትዮጵያን የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ በተመለከተ አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦች

የአንድ ሀገር ውጪ ጉዳይ መሠረታዊ ግብ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚኖራትን ግንኙነት መወሰን ነው። የሀገራችንን የውጪ ጉዳይ አቋምና ፖሊሲ አቅጣጫዎች ከመወሰናችን በፊት ግን በቀደሙት ሥርዓቶች የተከተልናቸው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲዎች ያስገኛቸውን መልካምና ክፉ ለውጦች በሚገባ መገምገም አስፈላጊ ነው። ባለፉት ሥርዓቶች አገራችን የተከተለቻቸውን ፖሊሲዎች በሰፊው ለመገምገም የሚያስችሉ በቂ ጥናቶችና መረጃዎች ባይኖሩንም በነዚህ ሥርዓቶች በዲፕሎማሲው መስክ ሲያገለግሉ የነበሩና በጡረታም ሆነ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ባለሞያዎችን ጊዜው ሳይረፍድ በማሳተፍ የመረጃና የጥናት እጥረቱን ማሟላት ይገባል። ለዚህ ጽሑፍ አመቺ እንዲሆን በሀገራችን የቀደሙ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲዎች ላይ በግልና በመንግሥት ተቋማትና ግለሰቦች የተሰሩ ጥናቶችን በማመሳከር ኢትዮጵያ እስከዛሬ የተከተለችው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንደሚከተለው መገምገም ይቻላል።

### ታሪካዊ አመጣጥ

በሀገራችን ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ተቀርጾ መተግበር እስከጀመረበት የዳግማዊ አፄ ምኒሊክ መጨረሻዎቹና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መጀመሪያ የሥልጣን ዘመን ድረስ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን በመሪዎቹ ስብዕናና የግል ፈቃድ ላይ እንዲሁም በጥቂት የውጪ ሀገር ልምድና ቋንቋ ችሎታ ባላቸው አማካሪዎች ሃሳብና አገልግሎት ላይ የተመሰረተ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት የሀገራችን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ በቋሚ የፖሊሲ አቅጣጫ የሚመራ ሳይሆን ጊዜ ያመጣቸውን ተለዋዋጭ ጥቅሞችና ጉዳቶችን በማስተናገድ ላይ የተመሠረተ ነበር። ለዚህም በወቅቱ ያጋጠማቸውን የካቶሊካውያንን ሰፊ ተፅዕኖ ለመቋቋም በአፄ ሱሴንዮስ የኢትዮጵያን ድንበሮች ለውጪ ሀገር ዜጎች ዝግ የማድረግ ውሳኔ፣ ዘግይቶም ቢሆን በአፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ መሐመድ ጋር የነበረው ጦርነት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የሀገራችን ‹‹ማዕከላዊ መንግሥት›› በተዳከመበት ወቅት የተለያዩ የሥልጣን ተቀናቃኞች ለውጪ ኃይሎች የሚያደርጉት የድጋፍ ጥሪ እንደ ሀገራዊ ዲፕሎማቲክ ድል ለመውሰድ ባይቻልም የሀገራችን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ፍላጎት እና ዓይነት ሥፋትን ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም በአፄ ቴዎድሮስ የውጪ ጉዳይ ግንኙነት ፍላጎቶች ሳቢያ የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ወረራ ድረስ በሀገራችን የተከሰቱ ዋና ዋና የታሪክ ሂደቶችን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

ዘመናዊ አሠራርን ለሀገራችን የማስተዋወቅና የሀገራችንን ድንበሮች በሁሉም አቅጣጫ የማካለል ጽኑ ፍላጎት የነበራቸው ዳግማዊ አፄ ምኒሊክም በኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ካሳደሯቸው ከፍተኛ ተጽዕኖዎች መካከል የአድዋ ጦርነትን ድል መሪነትንና የሀገራችንን የመጀመሪያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር መሰየማቸውን ዋነኞቹ ናቸው። ይሁንና ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅራዊ ሆኖ መተግበር የጀመረው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሲሆን ይህም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በሰው ኃይልና በገንዘብ በማጠናከር በጥናትና በጽሑፍ ላይ የተመሠረት አሠራር ላይ የተመረኮዘ መሆን በመጀመሩና የውጪ ሀገር እንደራሴዎችና ኤምባሲዎች በመደራጀታቸው ይገለጻል። ሆኖም በጣሊያን ወረራ ወቅት የመንግሥት አስተዳደር ሂደት ለተወሰኑ ዓመታት ከተቋረጠባቸው አምስት ዓመታት ባሻገር የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪና የከፍተኛ ባለሥልጣናትና የውጪ እንደራሴዎችን ሿሚና ሻሪ ንጉሡ በመሆናቸው የአገራችን የውጪ ጉዳይ በፖሊሲ የሚመራ ነበር ለማለት አያስደፍርም።

በደርግ ዘመነ መንግሥት የውጪ ጉዳይ አስተዳደር በገንዘብ፣ በመዋቅርና፣ በኤምባሲ ብዛትና በሰው ኃይል ከቀደመው መንግሥት አንጻር መዳበሩ ባይካድም ከፖሊሲ ይልቅ በፖለቲካ መመራቱና በመሪ የግል ፍቃድ ተከትሎ ከማዘመም አልዳነም። ይሁንና ዛሬ ለምንከተለው የሀገራችን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ከቀደሙ ሥርዓቶች የምንወርሳቸው ጉዳዮች መኖራቸው አይካድም።

በዚህም መሠረት ነጻነታችን፣ የሀገራችን ድንበሮች፣ የባሕር ጠረፍና ወደባችን፣ ጥንታዊ ባሕላዊና ኃይማኖታዊ እሴቶች፣ ቅርሶች፣ ቋንቋዎችና ተቋማቶቻችን በአሉታዊ ተጽዕኖ ሳይዳቀሉ ወይም ሳይጠፉ ለዛሬው ትውልድ መቆየታቸው፣ ዓለም አቀፍ እውቅና ማትረፋቸው፣ የበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት መሥራች ሀገር መሆናችን፣ የአፍሪካ ሕብረት ጠንሳሽና መቀመጫ መሆናችን፣ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የመሠረትናቸው የንግድና የውጭ ግንኙነቶችና ሀገራችን ያፈራቻቸው ምሁራንና የልዩ ልዩ መስኮች ባለሞያዎች ያተረፉልን ዓለማቀፋዊ መልካም ዝና የምንኮራባቸውና ጠብቀን ከምናዘልቃቸው ጥንካሬዎቻችን መካከል ናቸው። በተለይ ደግሞ ቡናን ማዕከል አድርጎ ለሀገራችን የግብርና ምርቶች የውጪ ገበያ መንገድ መጠረጉና በተጓዳኝ በሀገራችን ለውጪ ሀገራት የቴክኖሎጂ፣ የአገልግሎትና የምርት የገበያ በር መከፈቱ ታሪካዊ የውጪ ጉዳይ ሂደታችን ያስገኘልን ውጤት መሆኑ አይካድም።

በአንጻሩ በሀገራችን ውስጣዊ ሁኔታም ሆነ በአካባቢያዊ ወይም በዓለም ፖለቲካዊ ሁኔታ ሳቢያ በሀገራችን የውጭ ጉዳይ ግንኙነት ላይ ያጋጠሙ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ማረምና እንዳይደገሙ መከላከል ያስፈልጋል። በድርቅና በእርዳታ ተቀባይነት፣ የሀገራችንን ድንበሮች ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚያጸኑ ስምምነቶች አለመኖር ወይም ክፍተት፣ በእርስ በርስ ግጭትና በአካባቢ ጦርነት፣ ለእያንዳንዱ የዓለም ኮሽታ ከፍተኛ ተጋላጭነታችን የአገራችንን ተቀባይነትና ሚና ካሳነሱብን አሉታዊ ጎኖች መካከል ጠንካራ እርማት ሊደረግባቸው ከሚገባ ጉዳዮች ጥቂቶቹ ናቸው። ዲሞክራሲ ባልሆነ ሥርዓት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ጋር ተዳምሮ በአሠራር፣ በሰው ኃይልና የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሩ መዋቅርና አደረጃጀት በግለሰብና

በፖለቲካ ከፍተኛ ተጽዕኖ ስር መውደቅ እንዲሁም በአገራችን የገንዘብ አቅም ሳቢያ የሚመጡ መጥፎ ጎኖች መታረም ካለባቸው ሁኔታዎች የሚካተቱ ናቸው።

## የኢሕአዴግ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ውጤቶች

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ጥናት ሲደረግበት ቆይቶ በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እንደሚቀርብ የተነገረው ረቂቅ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ሰነድ፣ አገራችን ለ20 ዓመታት ገደማ (ከ1994 እስከ 2012 ዓ.ም) ስትከተል የቆየችውን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ እንደሚያሻሽል ተገልጿል። ማሻሻያ ያስፈለገው አሁንም በሥራ ላይ የሚገኘው ፖሊሲና አካሄድ ድክመቶችና ክፍተቶች እንዳሉበት በመታወቁ እንደሆነ ስለሚገመት በነዚህ ነጥቦች ላይ ሰፊ ዝርዝር ለጊዜው ወደ ጎን ማለት ይቻላል።

ከ1994 ዓ.ም እስከ ዛሬ ድረስ በአካባቢያችን፣ በአህጉራችንና በዓለም ላይ በርካታ ለውጦች ተከስተዋል። አዳዲስ ተገዳዳሪ ኃያል ሀገራትና ቡድኖች ተበራክተዋል፣ ያደጉ ሀገራት ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ተቀያይረዋል፣ አዳዲስ ስጋቶች መጥተዋል እንዲሁም የውጪ ጉዳይ ግንኙነት መርሆችና መሳሪያዎች ተለውጠዋል። አዳዲስ ሀገራት ተመስርተዋል። ዓለማችን ዛሬ የምትገኝበት የቴክኖሎጂ፣ የአሠራርና የሙያ ብቃት እንዲሁም የእድገትና የዘመናዊነት መመዘኛዎች ደረጃ ብቻውን ለ17 ዓመታት የተገለገልንበትን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ለማሻሻል ያስገድደናል። የአንድ ሀገር የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ጽኑነት/ቋሚነትንና (rigour/permanence) ተለዋዋጭነትን (adaptability) በእኩል ደረጃ ማስኬድ መቻል አለበት የሚለውን መሰረታዊ መርኅ የሚያጠናክር ነው።

የኢሕአዴግ መንግሥት የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ከኤርትራ ጋር በነበረው ጦርነትና የግንኙነት መቋረጥ፣ በሶማሊያ ባሰማራነው ጦር፣ ወደ አረብ አገራት ለጉልበት ሥራ በሚሰደደው የሰው ኃይል ብዛት፣ በከፍተኛ ስደተኛ አመንጪ ሀገርነት፣ በዓለማችን ከሚገኙ ከፍተኛ እርዳታ ተቀባይ ሀገራት አንዱ በመሆንና በተለይ ወደብ አልባ ሀገር በማድረጉ በዋናነት ይገለጻል። እንዲሁም ከሥርዓቱ አምባገነንነት ባሻገር በብሔር ተኮር ሀገራዊ አደረጃጀቱና መንግሥታዊ አሠራር ሳቢያ እንዲሁም ከኤርትራ እና ከአዲሷ ጎረቤት ሀገር ደቡብ ሱዳን የድንበር ማካለል ሥራ አለመሠራቱ ከቀደሙ መንግሥታት በወረስናቸው የውጪ ጉዳይ ድክመቶች ላይ ተጨማሪ ውስብስብ የአሰራር፣ የይዘት፣ የአቅምና የግንኙነት እክሎች አስከትሎብናል።

በሌላ ወገን በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመን በንድፈ ሃሳብ የቀረውን የአባይ ግድብ መተግበር ማስጀመሩ፣ ኤርትራ በሀገራችን የነበራትን አላስፈላጊ የኢኮኖሚ ጥገኝነትና በሀገራችን ላይ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ተጽዕኖ በኃይልም ቢሆን ማስቀረቱ፣ ሀገራችን በሰላም ማስከበርና በስደተኛ ተቀባይ ሀገርነት ያተረፈችው መልካም ስም፣ አዳዲስና ሰፋ ያላቸው የንግድ መስመሮች መከፈታቸው ጥሩ ጎኖች ናቸው። በተጨማሪም የአፍሪካ ሕብረት ተቀማጭነት ከኢትዮጵያ እንዳይነጠቅ የተደረገው ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ትግልና ድል፣ በሀገራችን የተከፈቱና ሀገራችን የከፈተቻቸው ኤምባሲዎች ቁጥር መበራከት፣ የአክሱም ሃውልትና ሌሎች ቅርሶቻችን መመለስ፣ ተቀማጭነታቸውን ወይም ቅርንጫፎቻቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉ አዳዲስ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መበራከታቸው፣ በተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የሀገራችን ተሳትፎና አባልነት መጨመር መዘንጋት የሌለባቸውና ሊጠናከሩ የሚገቡ መልካም የኢሕአዴግ ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው። በነዚህ ዓመታት በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ ቅርሶችና ሃብቶችም በዚህ ዝርዝር ውስጥ የሚካለሉ ናቸው። የፖሊሲና የአቅጣጫ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ሲደረግ በእውቀትና በጥናት የታቀፈ መሆን የሚገባው ሀገራችን ባላት ውስን የሰውና የገንዘብ አቅም የገነበነውን ጠንካራ ጎን እንዳናባክን ስለሚረዳ ነው።

የተሻሻለው ረቂቅ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እስከሚጸድቅ በሥራ ላይ የሚቆየው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ የተገነባበት ዋና ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲ ሲሆን የውጪ ጉዳይ ግንኙነታችን በአብዛኛው የተማከለው ደግሞ በኤርትራ ላይ በነበረን አቋም ነበር። በዚህም መሠረት አብዛኛው የዲፕሎማሲያችን ውስን የገንዘብና የሰው ኃይል አቅም የሚውለውና አሠራር የሚገመገመው ከሌሎች ሀገራት በንግድም ሆነ በእርዳታ በመጣው ገንዘብና ከኤርትራ ጋር የነበረውን stalemate በማስቀጠል ወይም justify በማድረግ ነበር ማለት ይቻላል። ይህ አካሄድ በአሠራርና በዲፕሎማሲያዊ የሰው ኃይላችን አቅምና አሠራር ላይ ካስከተለው ጤናማ ያልሆነ ተጽዕኖ ባሻገር ሀገራችን በውጪ ከሚኖሩ ወገኖቿ ጋር የነበራትን ግንኙነት በዜግነት ሳይሆን በገቢ ምንጭነትና በሌሎች ተገቢ ባልሆኑ መመዘኛዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርጎታል። በተለይም ደግሞ ይህ በአደገኛ ደረጃ ወደ ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲ ያጋደለ ፖሊሲ በሀገራችን ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ ሃብትና እሴቶች ላይ ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎናል።

## የፖሊሲ አቅጣጫ ሃሳብ

### ሀ) የፖሊሲው መርሆዎች

1. ስለዚህ ለኢትዮጵያ አዲስ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ መቅረጽ እንደሚያስፈልግ እናምናለን። ከላይ ከጠቀስናቸው ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ባሻገር አዲስ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲው የሀገራችንን የሕዝብ ቁጥርና የዕድሜ ክልል፣ የወጣት ሥራ አጥ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሄድና የሀገራችንን ምጣኔ ሃብት ሰፊ ድርሻ የሚይዘው አሁንም ግብርናው ቢሆንም በተለይ በደካማው ግብርናችን ላይ የተጋረጡትን አዳዲስ አደጋዎችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር የምንከተለው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ የሀገራችንን ሕዝብ የሚወክል/የሚመስልና የሕዝቡን ጥቅም የሚያስከብር/የሚያስቀድም መሆን አለበት።
2. የማንኛውም ግንኙነት መሠረት የሆነውን፣ ከጎረቤት ሀገራቶች ጋር አብሮ ለመኖር የሚያስችለንን እንዲሁም ለዓለማቀፍ ተቀባይነታችን (global standing) ወሳኝ የሆነውን ሰላምን መፍጠርና ሰላምን ማበልጸግ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን ማዕከላዊ መርህ (central principle) ነው።
3. እንዲሁም ዴሞክራሲንና ግልጽነትን የሚያጎለብቱ ግንኙነቶችንና አሠራሮችን ማበራከት፣ መፍጠር፣ ማጠናከር ለዚህም የሚረዳንን አስተዳደራዊና ዲፕሎማሲያዊ አቅም መጨመር የውጪ ጉዳያችን መርህ አካል መሆን አለበት።

### ለ) የፖሊሲው መለኪያዎች

1. የሀገር ውስጥ ሁኔታ የውጪ ጉዳይ ግንኙነታችን ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የታወቀ ነው። ይሁንና የሀገራችን ውስጣዊ ሁኔታ በውጪ ጉዳይ ግንኙነታችን ተጽዕኖ ሥር እንዳይወድቅ መጠበቅ የፖሊሲያችን ስኬት ዋና መለኪያ መሆን አለበት። የአንድ ሀገር ሉዓላዊነትና ክብር የሚመዘነው በውጪ ጉዳይ ፖሊሲው ሀገርን ከአሉታዊ ባዕድ ተጽዕኖ የመከላከል አቅም ነው ።

2. ሌላው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን ስኬት የአገራችንን ሕዝብ ማዕከል ያደረገ ዘላቂ የንግድና ኢንቨስትመንት መስመሮችን መዘርጋትና ማጠናከር ነው። ሕዝባችንን ማዕከል ያደረገ የንግድ ግንኙነት ስንል በቁጥር ብቻ የሚሰላና ለሕዝብ ተደራሽነቱ ደካማ የሆነ ወይም የመንግሥትንና/የጥቂቶችን ካዝና የሚያጎለብት የኢኮኖሚ እድገት የሚያስመዘግብ ሳይሆን የሕዝቡን ኑሮ የሚያሻሽል፣ የብዙኃኑን የገንዘብ አቅምና ክኅሎት የሚያጎለብት የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ማለት ነው። እንዲሁም በዘላቂነት በዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሠረት የሚገመገምና የሀገራችንን ተፈጥሮ ሃብት፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ እድገት፣ የሕዝቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል ማለት ነው። በዚህም መሠረት የሀገራችን ዲፕሎማሲ የሚያስገኛቸው ውጤቶች በዘላቂነታቸውና በሕዝብ ጠቀሜታቸው እንጂ በብዛታቸው የማይለኩ ይሆናሉ ማለት ነው።

3. በመጨረሻም የሀገራችንን ጠንካራ ጎኖች፣ እሴቶችና ሃብቶች በዓለምና በአካባቢያችን ማስተዋወቅና ማሰራጨት ሌላው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ግባችን መሆን አለበት። ይህም ከቀደሙት የዲፕሎማሲ ግንኙነቶቻችን የወረስናቸውን በመጠበቅ ሁሉም ቅርሶቻችንና ሃብቶቻችን እውቅና እንዲያገኙ ከማድረግ ጀምሮ በሰላም ማስጠበቅም ሆነ በዓለም አቀፍ መድረኮችና ተቋማት ተሳትፎን በማጠናከር እንዲሁም የጥናትና ምርምር ተወዳዳሪነታችንን በማጎልበትና በመሳሰሉት 'soft diplomacy' ተብለው በሚታወቁ የግንኙነት ዓይነቶች የሚገኝ ውጤት ይሆናል።

## ሐ) የፖሊሲው መገለጫ

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው የአንድ ሀገር የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ መንታ ባህሪዎችን ያቀፈ መሆን አለበት። በአንድ በኩል ከሉዓላዊነትና የሀገር ክብር የተቆራኘ በመሆኑ በሀገር ውስጥ ፖለቲካ ተለዋዋጭነትም ሆነ በባዕድ ተጽዕኖ አላስፈላጊ ግፊት የማይናወጥ መሆን አለበት። በሌላ በኩል ዓለም ከደረሰችበት ሁሉ አቀፍ እድገት ደረጃና ተለዋዋጭ ስጋቶችና ተግዳሮቶችን ያገናዘበ እድገትና ለውጥ ማሳየት አለበት። እነዚህ መንታ ባህሪያትን አመጣጥኖ ማስኬድ የሚቻለው በዲፕሎማሲው የሰው ኃይልና በጠንካራ ተቋም ተደጋጋፊ እገዛ ነው። በቀላሉ ለማስረዳት ያክል የፖሊሲን ቋሚነት ማረጋገጥ የምንችለው የሀገራችን መንግሥታዊ ተቋማት ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነጻ ሆነው ማገልገል ሲችሉ ሲሆን ለወቅቱ ሁኔታ ተገቢውን ምላሽና ለውጥ ማካሄድ የሚቻለው ደግሞ በልምድም ሆነ በእውቀት ባለሙያ የሆነ የሰው ኃይል ሲኖር ነው። የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ በተለየ መልኩ ለተዛባ የቋሚነትና የተለዋዋጭነት ባህሪ ችግር ተጋላጭ ስለሆነ እንደምሳሌ ይጠቀስ እንጂ ማንኛውም ሀገራዊ ፖሊሲ ይህ መንታ ጠባይ ሊኖረው ይገባል።

ከዚህም ባሻገር የውጭ ጉዳይ ግንኙነታችንንም ሆነ ሌሎች ፖሲሲዎቻችንን በዚህ መልኩ መቅረጽና መፈተሽ የሀገራችንን ተቋማት በማጠናከር ወደ ዲሞክራሲያዊ አሰራር የሚደረገውን ሽግግር የሚያቀለውና፣ ለብዙኃኑ ግልጽ ከማይሆንና ውስን አቅማችንን ከሚያባክን የርዕዮተ ዓለምና የመርኅ ሽክምና ክርክር ያድናል የሚል እምነት አለን። ሀገራችን የምትከተላቸውን ፖሊሲዎችና አቋሞች ከግለሰብ ፍላጎትና መልካም ፈቃድ ተፅዕኖ ለማላቀቅም ሆነ የፖሊሲ አቅጣጫ ከላይ እስኪመጣ እጁን አጣምሮ ከሚጠብቅ የሰው ኃይል ለመታደግ እንደሚረዳ እናምናለን። የፖሊሲያችን መሪ ሃሳብ በፍጥነትና ወቅታዊ መፍትሄ የሚያቀርብ መሆን መቻል ነው።

### ይህንን መሠረት በማድረግ የፖሊሲያችን ዋና ዋና መገለጫዎች

- አገራችንን ከለማኝነት ወደ እኩል አጋርነት፣
- ከተጽዕኖ ተቀባይነትና ከፍተኛ ተጋላጭነት አላቆ ወደ ተፅዕኖ ፈጣሪነት
- እንዲሁም በሁሉም ሀገራት የተበተኑትንም ሆነ ሀገር ውስጥ ያሉ ዜጎቿን ወደ ማስከበር ማሸጋገር የሚሉት መሆን አለባቸው።

## መ) የፖሊሲው ቀዳሚ ተግባራት

1. ከጎረቤት ሀገራት ጋር የድንበርና የንግድ ግንኙነት የሚያጸና ግልጽ ስምምነቶች መፈራረምና ማካለል የውጪ ጉዳይ ቀዳሚ ሥራ ማድረግ በአካባቢያችን ላይ ከተንሰራፋው የሕገ ወጥ ሰውና መሳሪያ ዝውውር፣ ከግጭትና ከሽብር እንዲሁም ከሌሎች ድንበር ዘለል ወንጀሎች በዘላቂ ሁኔታ ለማስቆም መሠረታዊ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአገራችን የሚገኙ ስደተኞችን በተመለከተ የመካከለኛና የረዥም ግዜ እቅድ ከሚመለከታቸው ሀገራትና ተቋማት ጋር በመሆን በፍጥነት መነደፍ ይኖርበታል።

2. ባለፉት አስር ዓመታት የአገራችንን የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲ አቅም ያፈሰስንበትንና የሀገራችን ሕዝብ በተለያዩ መንገዶች ዋጋ የከፈለበትን የሕዳሴ ግድብ እቅድ ማስፈጸም፣ ለዚህም አስፈላጊውን የዲፕሎማሲና ተያያዥ ኃይል/አቅም መመደብ።

3. የአፍሪካውያን የሰውና የተፈጥሮ ሃብት ለመቀራመት የሚሽቀዳደሙ አዳዲስ ሀገራትን በሕብረት እንጂ በተናጠል መቋቋም እንደማይችሉና እንዲሁም የአፍሪካ ሕዝብ እንደ ቀደሙ ዘመናት በጥቂት አምባገነኖች ጉብኝነትና ኃፍረተ ቢስነት ሃብቱን ለባዕዳን ሲረከብ በዝምታ እንደማያልፍ በተለያዩ መንገዶች እየታየ ነው። ዛሬ የዓለም ሀገራት የደረሱበትን የእድገት ደረጃ ላይ በፍጥነት ለመድረስና ተወዳዳሪ ለመሆን፣ ካሉብን የኢኮኖሚ ድኅነት ችግር ላይ የተደረቡብንን ተጨማሪ ስጋቶችን (ስደተኝነት፣ ሥራ አጥነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የምግብ እጥረት፣ የከተሞች መስፋፋትና የገጠር ፍልሰት፣ የወጣት ቁጥር መብዛት፣ የሳይበር መረብና ሌሎች ወንጀሎች፣ የስደተኛ ተቀባይ ሀገራት ፖሊሲዎች መቀየር፣ ሽብርተኝነትና ጽንፈኝነት ወዘተ) የትኛውም አፍሪካ ሀገር በተናጠል ለመከላከልና ለመቋቋም አይችለውም። የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን ቅድሚያ የሚሰጠው አካባቢ አፍሪካ ነው መሆን ያለበት። ሀገራችን ከአካባቢዋና ከአህጉሯ የተለየ እጣ ፈንታ እንደማይኖራትና በአፍሪካ አንድነትና መጠንከር የምታምንና ይህንንም ለማስፈጸም ስትጫወት የኖረችውን ታሪካዊና ዲፕሎማሲያዊ ሚና አጠናክሮ ማስቀጠል። የሻከሩ ግንኙነቶችን ማደስ፣ በአፍሪካ ሕብረት የነበረንን ተሰሚነት መመለስ። የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን በገንዘብ እራሱን እንዲችል የሚደረገውን እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ መደገፍ፣ የሰላም እንቅስቃሴዎችንና ድርድሮችን ማበረታታት።

4. ከምዕራብ ሀገራት ጋር ያሉንን ጠንካራ ግንኙነቶች ማስቀጠል እንደሚያስፈልገው ሁሉ የምዕራብ ሀገራት የግንኙነት መርህ ከእርዳታ ወደ ንግድ በመሸጋገሩ እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች በመለወጣቸው ከነዚህ ሀገራት ጋር ያሉንን ሚስጥራዊም ሆነ ግልጽ የንግድ፣ የብድር፣ የገቢ፣ የእርዳታና ትብብር ስምምነቶች ለሕዝባችን ከሚያስገኙት ዘላቂ ጥቅም አኳያ እንደገና ማጥናት፣ መፈተሽ፣

መገምገም።

5. በማያያዝም ከዓለም አቀፍ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ጋር የተፈራረምናቸው የንግድ፣ የብድር፣ የትብብርና ሌሎች ስምምነቶች በባለሞያ ማስጠናት፣ መፈተሽና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ።
6. አዳዲስ ኃያላን ሀገራት በመሆን ብቅ ያሉ የእስያ፣ የደቡብ አሜሪካ፣ የምስራቅ አውሮፓም ሆነ የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ጋር የሚኖረንን አዲስ ግንኙነት ለመቅረጽ የሚያስችል በእውቀትና በልምድ ላይ የተመሰረተ ጥናት ማካሄድና መወሰን። እስካሁንም የተደረጉ ስምምነቶችን መፈተሽ።
7. እንዲሁም የሀገራችንን መደራደሪያ/ ጠንካራ ጎኖችንና ድክመቶችን አገናዝቦ በሀገራችንና በአካባቢያችን ላይ ያንዣበቡ ነባርና አዳዲስ ስጋቶችንና ተጽዕኖ ፈጣሪ ኃይሎችን የሚያጠና፣ የሚከታተልና፣ መሪ ሃሳብ የሚያመነጭ የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም ማደራጀት/ ማቋቋም የሚሉት የፖሊሲው ቀዳሚ ተግባራት መሆን አለባቸው።

### ሠ) አሰራርና መዋቅር

በአሁኑ ወቅት የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን አስፈጻሚ አካል የሚከተለው አሠራርና አደረጃጀት ማሻሻያዎች ሊደረግበት ይገባል። በቀዳሚነት የዲፕሎማሲውን የአሠራር ሂደቶችንና የሥራ ውጤት መመዘኛ ከላይ በዘረዘርናቸው መርሆዎች አንጻር መነደፍና መገለጽ ይኖርባቸዋል። በግልጽ ለውይይት ቀርበው በታመናበቸውና መስማማት በተደረሰባቸው መመዘኛ መሰረት የሚደረጉ ውሳኔዎችን በፍጥነት መተግበር ያስፈልጋል።

በተጓዳኝ በተለይ ባለፉት አስር ዓመታት የሚታዩ የውጪ ጉዳይ ኃላፊነትን በተመለከተ በአስፈጻሚው አካልና በሥሩ ያሉ መዋቅሮች መካከል፣ በመንግሥት ተቋማት መካከልና በውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ውስጥ ጭምር በሚታዩ የሥራ ክፍፍል ውዥንብሮች ማጥራትና በተለያዩ አካላት መካከል ያለውን የሥራና የኃላፊነት ክፍፍል ፈትሾ በግልጽ ማዋቀር ያስፈልጋል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ የተለያዩ መደበኛና ጊዜያዊ ወይም ተለምዷዊ መዋቅሮችና ተቋማት ተበራክተዋል፣ እንዲሁም በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ አካላት፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የጥናት ማዕከላት ቁጥር ጨምሯል። ስለዚህ ሁለገብ የሆነ የመዋቅርና የአደረጃጀት ጥናትና እርምጃ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል የሀገራችን አቅም ውስን በመሆኑ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊነት ከዓለም ሁኔታ ተለዋዋጭነትና ከውጪ ጉዳይ ግንኙነት መንገዶች ውስብስብነትና ቁጥር መጨመር ጋር የሚመጣጠን አልሆነም። ስለዚህ ያለብንን የሰውና የገንዘብ አቅም ክፍተት ለመሙላት ለጊዜው የተለያዩ አዳዲስ አሠራሮችን መዘየድ ያስፈልጋል። እነሱም የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሩን በሴክተር መሥሪያ ቤቶች መደገፍና መናበብ የሚያስችላቸው የግንኙነት መስመሮችን መክፈት፣ መሥሪያ ቤቱ ከሀገራችን የቋንቋና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ያለውን ትስስር የሚያጎለብትና አስፈላጊ ሲሆን የሚያስገድድ አሰራር ማስቀመጥ እና የመሳሰሉት ናቸው። የኤምባሲዎቻችንና የቆንስላም ሆነ ሌሎች ጽሕፈት ቤቶቻችን የገንዘብና የአሠራር ኃይል አጠቃቀም (efficiency) የሚያሻሽሉና አክለውም በውጪ ሀገር ከሚኖሩ ዜጎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት በሚያጎለብቱ ዘዴዎችን በፍጥነት ተግባራዊ ማድረግ የሚሉት በውጪ ጉዳይ ፖሊሲያችን አተገባበር ዙሪያ ከምናቀርባቸው ዝርዝር ማሻሻያዎች ጋር የሚያያዙ ይሆናሉ።

## ማጠቃለያ፡-

ባለፉት 20 ዓመታት የተከተልነው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲን በተመለከተ ዋና ትችታችን የዲፕሎማሲያችን አገልጋዮችንም ሆነ የተቋሙን አጠቃላይ የሥራ ስኬት ወይም ውጤት መመዘኛው፣ መገምገምያው እና መስፈርቱ የተዛባ መሆኑ ነው። ግለሰቦቹም ሆነ የሀገራችን ዲፕሎማሲ በሙያ ሳይሆን በፖለቲካ ታማኝነት፣ በሕዝብ ጥቅም ሳይሆን በገንዘብ ተኮር ግምገማ ሲንገላቱ ቆይተዋል። እንደቀደሙት የመንግሥት ሥርዓቶች ሁሉ ማንኛውም የተገኘ ሀገራዊ የዲፕሎማሲ ትግል ውጤት የሕዝብ ድል ሳይሆን የአንድ ፓርቲ፣ ብሎም የአንድ ግለሰብ/መሪ ድል ተደርጎ ሲወሰድ፣ ዲፕሎማሲያዊ ክሽፈቶች ደግሞ ግልጽ ባልሆነ ፓርቲ ተኮር ግምገማ ሲደባበሱና ሲሸፋፈኑ ቆይተዋል። ኢኮኖሚና ገንዘብ ተኮር የሆነ መመዘኛ ዲፕሎማሲያችንን አጎብዳጅና የሕዝብን ሉዓላዊነትና ክብር የሚነካ፣ በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዜጎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ጤናማ እንዳይሆን ያደረገ ሆኖ ቆይቷል። የመንግሥታቱ መሪዎችም ከሀገር ውስጥ ገጽታቸው ይልቅ በውጭ ሀገር ለሚኖራቸው ገጽታ ሲጨነቁ ኖረዋል፣ ዲፕሎማሲውም የግለሰቦቹን ገጽታ በማግነን ሽምያ ሲጠመድ ይታያል።

የሀገር ክብር፣ ህልውና ወይም ግንባታ፣ ሉዓላዊነትና ኢኮኖሚ በውጪ ጉዳይ አይገነባም፣ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ማዕከልና የመጨረሻ ግብ ሊሆኑ አይችሉም። የሀገር ግንባታን፣ ኢኮኖሚንና ክብርን የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ አቅጣጫ አድርጎ ማስቀመጥ የሀገርን ዜጋ ከውጪ ሀገር ዜጎች በታች የሚያደርግና በአገራችን ውስጣዊ ጉዳይ ላይ ባዕዳን እንዲወስኑ በር መክፈት ማለት ነው። በተግባርም እንዳየነው ዛሬ ዲፕሎማሲያችን ኢኮኖሚያችንን ለከባድ የብድር ዕዳ፣ ለተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣ ለግብር ኢፍትሃዊነት፣ ለሕገወጥ የገንዘብ ፍልሰት፣ ከውጪ በምንዛሪ በሚገዙ ግብዓቶች ጥገኝነት፣ በዚህም ሳቢያ ለሚከሰት የገንዘብ አቅም መዋዥቅና የኑሮ ውድነት፣ ከዛም የብድር ዕዳ ስረዛ ልመናና እርዳታ ጥገኝነት ዳርጎታል። ስለዚህ የሀገር ክብርና ህልውና ወይም ኢኮኖሚ የዲፕሎማሲው ስኬት መመዘኛ እንጂ ግብና ዓላማ ሊሆኑ አይችሉም።

ይሁንና የአንድ ሀገር ዲፕሎማሲያዊ ሥራ የሚጠይቃቸውን ክህሎቶች፣ ልምዶችና እውቀት በአጭር ግዜ ሥልጠና፣ ወይም ባማረ ንግግር የሚገነባ ስላልሆነ፣ በሴክተሩ ሀገራችን ያፈራቻቸውን ባለሞያዎች ወደ አዲሱ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ሃሳብ በአዲስ መንፈስ ይዘን ለመጓዝ ግድ ይለናል። በዘርፉ ሲያገለግሉ የነበሩ ባለሞያዎች እውቀትና ልምድ መባከን የለበትም። ለዚህም ቀላሉና አቅም አገናዛቢው መንገድ ባለድርሻ አካላቶችንና ሕዝብን ያሳተፈ አዲስ የስኬት መስፈርቶች መንደፍና መተግበር ነው።

እንደ ኢዜማ በዝርዝር አጥንተን የምናቀርበው የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ቁልፍ ሃሳብ ወደ ሕዝብና ዘላቂ ጥቅም ተኮር ዲፕሎማሲ አሠራርና መመዘኛ መስፈርት መመለስ ነው። ዜግነትና ማኅበራዊ ፍትህ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችንም መመሪያ ማድረግ ማለት ነው። ግንኙነቶቻችንና ስምምነቶቻችን ወጣት ለሆነው፣ በግብርና ለሚተዳደረውና በድኅነትና ሥራ አጥነት ለሚሰቃየው ብዙኃን በሚያስገኘው የክህሎት፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ ወይም የተፈጥሮና የኢኮኖሚ ጥቅም አኳያ ዳግም መፈተሽ አለባቸው። በውጪ ሀገር ከሚኖሩ ዜጎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ለማደስ እና የሕዝባችንን አገራዊ ኩራት ለመመለስ፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶቻችንን ከብዘት ይልቅ በጥራታቸው መፈተሽ አለባቸው። እንዲሁም ከታሪካችንም ሆነ ዛሬ በተግባር እንደምናየው የኢትዮጵያ ቁልፍ የዲፕሎማሲ እሴት/ሃብት/ መደራደሪያ ካርታ (diplomatic competitive advantage) አቀማመጧ ነው፣ አህጉሯ ነው፣ አፍሪካ ነች። ድክመታችን ሳትሆን ጥንካሬያችን፣ ድኅነታችን ሳትሆን ሃብታችን የሆነችውን አፍሪካን ማዕከል ያደረገ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ወደ ክብር፣ ወደ ሉዓላዊነት ወደ ማኅበራዊ ፍትሕ ይመልሰናል።

# ዜግነትን መሠረት ያደረገ

# ፖለቲካ እና ምርጫ




አሁን የመሸጋገሪያ ጊዜ ላይ ነው ያለነው፡፡ ወዴት እንሂድና እንዴት እንሂድ የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ የምንችለው የሄድንባቸውን መንገዶች ችግራቸው ምንድን ነው? የሚለውን ካወቅን በኋላ ነው፡፡ እነዛን ችግሮች መድገም የለብንምና! ሦስት ሥርዓቶች አልፈናል፡፡ የጃንሆይ፣ የደርግና የሕወሃት/ኢሕአዴግ ሥርዓት፡፡ በጃንሆይ ጊዜ የመንግሥት ሥርዓት ማለት ለንጉሥ የሚሰጥ፣ ንጉሡ ደግሞ በእግዚአብሔር የተቀቡ እግዚአብሔር እሳቸው ነው መንገሥ ያለባቸው ብሎ መርጦ ያስቀመጣቸው ሰው ናቸው፡፡ በዛ ዓይነት ሥርዓት መንግሥትና ንጉሡ አንድ ናቸው፡፡ መንግሥት ማለት ንጉሡ ናቸው፡፡ ንጉሡ ማለት መንግሥት ናቸው፡፡ በዛ ሀገር ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ሥራ በንጉሡ መልካም ፍቃድ የሚሆን ነው ማለት ነው፡፡ ከጃንሆይ ሥርዓት በኋላ የመጣው በእግዚአብሔር ተቀባው ብሎ የሚያምን ሳይሆን በማርክስና በሌኒን ተቀባው ብሎ የሚያምን ወታደራዊ አምባገነን ሥርዓት ነው፡፡ ያም ሥርዓት ከመንግሥቱ ኃይለማሪያም ውጪ ለኢትዮጵያ የሚያስብላት የለም ባይ ነበር፡፡ ከዛም በኋላ የመጣው የሕወሃት/ኢሕአዴግ ሥርዓት በመሠረታዊ እምነቱ የሶሻሊዝም አስተሳሰብ ቢይዝም ዋናው የማንነት መለኪያ ዘር ነው ብሎ፣ ሕዝብን በዘር ከታትፎ በሥልጣን ላይ ለ27 ዓመታት ቆየ፡፡ አንዱ በአንዱ ላይ ችግር እየጨመረ ነው እዚህ የደረስነው፡፡ ታዲያ አሁን ምን ዓይነት ሥርዓት ነው በሰላም የሚያኖረን? ወደ ብልፅግና የሚወስደንስ ምን ዓይነት ሥርዓት ነው? የሚል ጥያቄ ነው ከፊታችን የመጣው፡፡

ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለምንለው ዋና መለኪያ ነው፡፡ ስለዚህም ስለምርጫ ጥቂት ልበል፡፡

## ምርጫ ቢያንስ 5 ዋና ዋና ነገሮች ይሰጠናል፡፡

1. መሠረታዊ በሆነው የሥርዓቱ ምንነት ላይ የጋራ ስምምነት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ እንደማኅበረሰብ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጬ ምንድን ነው? በሚለው ላይ የጋራ ስምምነት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ የመንግሥት ኃላፊነትና ሥልጣን መሠረት ሕዝብ በነፃነትና በፍቃዱ በመረጠው ሰው ይሆናል፡፡ ለሁሉም በዛ ማኅበረሰብ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የጨዋታውን ሕግ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ ሥልጣን የሚመኙ ሰዎች በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሥልጣን ሊያገኙ የሚችሉት የሕዝብን ፍቃድ ያገኙ ብቻ እንደሆነ ያደርጋል፡፡ ይሄ በጣም ጠቃሚ ስምምነት ከመሆኑ በተጨማሪ የጨዋታውን ሕግ በግልፅ ያስቀምጠዋል፡፡
2. በመንግሥትና በማኅበረሰቡ መሀል የሚኖረው ግንኙነት ግልፅ የሆነና ተአማኒነት የሚኖረው ይሆናል፡፡ ማ ማንን ይወክላል? በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ

ብሔር በሙላ ወኪልህ ነኝ የሚል ድርጅት አለ፡፡ ያንን ውክልና ማን ነው የሰጠው? በምን ዓይነት መንገድ ነው የሰጠው? ይሄንን ግልፅ የሚያደርግ ነገር የለም፡፡ ለምሳሌ አንዱ ተነስቶ እኔ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ነኝ ስለዚህም የኦሮሞ ሕዝብን እወክላለሁ ይላል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ድምፅ ሰጥቶ ትወክለኛለህ አላለው፡፡ እኛ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ እንላለን፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች ፓርቲ ነን ስንል የኢትዮጵያ ዜጎች በሙሉ እንወክላለን ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ ምርጫ የሚጠቅመው የሕዝብ ወኪሎች እነማን ናቸው የሚለውንም ለመለየት ነው፡፡ በጨበጣ የሕዝብ ወኪል ነኝ ማለት ይቆማል፡፡ ያለ ነፃ ምርጫ ምንም ዓይነት የሕዝብ ውክልና አይኖርም፡፡ የሕዝብ ወኪል ነኝ ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው ሕዝብ ያለፍርሃት በነፃነት መርጦ ወክለኝ ያለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

3. ለውጥን በሰላማዊ መንገድ ለማስተናገድ ለወደፊትም ዕድል ይሰጣል፡፡ ማኅበረሰባችንን ከውስጥም ሆነ ከውጪ የሚመጡ ግፊቶች ለችግሮች ሊዳርጉት ይችላሉ፡፡ ምርጫ ተደረገ ማለት የማኅበረሰባችን ችግሮች ተፈተዋል ማለት አይደለም፡፡ የሥራ አጥነት፣ የድህነት፣ የመኖሪያ ቤት ችግር፣ የሕክምና ችግር ወዘተ.... አለብን፡፡ እነዚህን ሁላ ለመፍታት ነው የምንሄደው፡፡ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ማኅበረሰባችን ችግር ውስጥ ሲገባ ይሄንን የምርጫ መንገድ ከተለማመድን ከዛ በኋላ ችግሮቻችንን የምንፈታበት ዘላቂ የሆነ መንገድ ይሰጠናል፡፡ ስለዚህም ለውጥ ለማምጣት ወደ ግጭትም ሆነ ወደ ጦርነት መግባት አይኖርብንም፡፡ ለውጥ ከፈለግንና ያለፈው ካልተስማማን ምርጫ ጠብቀን ሌሎችን የምንመርጥ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሕዝብ ለውጥ ሲፈልግ ጦር መማዘዝ፣ መደባደብ፣ መገዳደል የለበትም፡፡ በሕግ በተሰጠው የመምረጥ መብት ተጠቅሞ አዲስና የተሻለ ነገር ያመጣል፡፡

4. ወደ እውነተኛና የመንፈስና የሀሳብ ሥልጣኔ ይወስደናል፡፡ ከፖለቲካ ውጪ በሚኖሩ ጉዳዮች ላይ ችግሮችን በሠለጠነ መንገድ በውይይት በሕግ የመፍታት ባሕላችንን እያበለፀግን እንሄዳለን፡፡ ችግሮች ሲኖሩ ችግሮችን በሕግ መፍታት የምንችልበት አዲስ ምዕራፍ ይሰጠናል፡፡

5. የአንድ ፖለቲካ ማኅበረሰብ አባላት መሆናችንን በተግባር ያረጋግጥልናል፡፡ ማኅበራዊ ግንኙነታችንን ያጠናክርልናል፡፡ የሀገር ፍቅራችንን ያበለፅገዋል፡፡ አንድነታችንን በጠንካራና ምክንያታዊ መሠረት ላይ ያኖረዋል፡፡ እስከዛሬ ኢትዮጵያ አንድናት እያልን እናወራለን፡፡ በውስጧ ግን የታመቀ ፍትህ አላገኘንም ብለው የሚጮሁ ማኅበረሰቦች አሉ፡፡ ሁሉም እኩል የሆነበትን ይሄን የጨዋታ ሕግ አንዴ ከተገበርነው ማለትም ከታች አንስቶ እስከ ላይኛው የመንግሥት መዋቅር ያሉ የኃላፊነት ቦታዎች ሕዝብ በመረጠው ሰው የሚተዳደር ከሆነ ኅብረተሰቡ የአንድ ፖለቲካ ማኅበረሰብ አባል መሆኑን እያመነ ይሄዳል፡፡

## ዜግነት ምንድን ነው?

ዜግነት ማለት ሌላ ዓይነት የማንነት ስሪቶችን መበጠስ ማለት አይደለም፡፡ በማንነት መሰባሰብ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በአንድ የእግርኳስ ቡድን ደጋፊነት.... መሰባሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁላችንም በርካታ ማንነቶች አሉን፡፡ እነዚህን ሁላ ማንነቶች እንዳሉ ሆነው በጋራ በሆነ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ግን እነኛን የወል ዕምነቶቻችንን እንደተጠበቁ በጋራ እንድናስብ የሚያደርገን ማንነት ነው ዜግነት፡፡ ሆን ተብሎ የዜግነት ፖለቲካ ማለት ሁሉንም ለመጨፍለቅ የሚነሳ እሳቤ ነው ይባላል፡፡ ብለን አናውቅም፤ ልንልም አንችልም፡፡ ይህን የሚሉት ዜግነት ማለት ምን እንደሆነ የማያውቁ ወይም ማወቅ ያልፈለጉ ናቸው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ማለት በአንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ውስጥ እስካለን ድረስ መንግሥት የሚባለው ሁላችንንም በጋራ የሚወክለው አካል የእያንዳንዳችንን ከዜግነት ውጪ ያለ ማንነት እያየ አይደለም ለዛ ማንነት መልስ የሚሰጠው፡፡ ሁላችንንም በእኩልነት እንደ ዜጎች ነው የሚያየን የሚሆነው፡፡ ፖለቲካ በሚባለው የጋራ ጉዳያችን ላይ መሰባሰብ ያለብን አንድ በሚያደርገን ዜግነታችን ላይ ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ማለት ይህ ነው፡፡ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ስንሰባሰብ በጋራ በሆነው የዜግነታችን አንድነት ነው፡፡ በሀሳብ ግን የተለያየን ልንሆን እንችላለን፡፡ በጋራ ባለን የዜግነት ማንነትና የአመለካከት አንድነት ላይ ተመስረተን ነው ፓርቲ መመስረት ያለብን፡፡

የፊታችን ምርጫ ከዜግነት ጉዳይ ጋር እንዴት ነው የሚያያዘው ለምን አስፈላጊ ነው?

በሚመጣው ምርጫ ማኅበረሰቡ ያለምንም ፍርሀት የሚፈልገውን የሚመርጥበት ሆኖ ቢጠናቀቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ማኅበረሰቡ ወክሏቸው በስሙ የሚፈልገውን የሚናገሩለትን ሰዎች እናውቃለን፡፡ ያሉትን ችግሮች በውይይት ለመፍታት የሚቻለውም በሕዝብ ውክልና ያላቸው ቡድኖች የተወያዩ እንደሆነ ነው፡፡ አንዱና ትልቁ የምርጫ አስፈላጊነት ጉዳይ በጨበጣ የሚካሄደውን እወክልሀለሁ የሚለውን ጉዳይ እንዲቆም ያደርገዋል፡፡ በጨበጣ ሲሆን በስሜት እንጂ በምክንያት መግፋት አይቻልም፡፡ በስሜት ማነሳሳትና እውነተኛ ውክልና አግኝቶ ውክልና ለሰጠኝ ሕዝብ ምን ላድርግ ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ውክልና አግኝቶ ምን ላድርግ ማለት ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሕዝብን ወክሎ መናገር ለዛ ሕዝብ ኃላፊነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ያ ኃላፊነት ደግሞ ኅብረተሰቡን ማጋጨት አይደለም፡፡ ኅብረተሰቡ የሚፈልገውን ነገር አውቆ ምንድን ነው ጭንቀቱ? ያጣውስ ምንድን ነው? ምን ብናደርግለት ነው የሚሻለው? ብሎ በመጠየቅና ከሌሎች ጋር መደራደር ነው፡፡

ከፊታችን ያለው ምርጫ ላይ ፅንፍ የረገጠ አመለካከት ያላቸው ቡድኖች ኅብረተሰቡ ቢመርጣቸው ራሱ ቁጭ ብለው በፖለቲካ ማዕከል ውስጥ ገብተው መነጋገር ሲጀምሩ የሚፈልጉትን ነገር እንደማያገኙ ሲያውቁ ለድርድር ይቀመጣሉ፡፡ የሚመረጠው ሰው ራሱ ያሰብነውን የፈለግነውን ነገር በሙላ አያገኝልንም፡፡ ነገር ግን የሚመረጠው ሰው የመረጡት ሰዎች ጠበቃ በመሆን የመረጡትን ሰዎች ጥቅም እንዲከበር ሁልጊዜም የሚታገል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ያንን ካላደረገ በሚቀጥለው ምርጫ ይባረራልና፡፡ ይሄንንም የሚመረጠው ሰው ያውቃል፡፡ የሚመረጠው ሰውም መራጩን የሚፈራ ይሆናል፡፡ የሥልጣን ምንጩ መራጩ ነውና፡፡ ስለዚህም መራጮቹን ሊጎዳ የሚችል ነገር ሊያደርግ አይችልም፡፡ ተመራጩ አድልዎ ቢፈፅምም ከ5 ዓመት በኋላ ከቦታው እንዲባረር ይደረጋል፡፡ ይህ ነው ውክልና ማለት፡፡ ይህ አይነቱ አሰራርም ነው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያመጣልን፡፡

ይህ ጽሑፍ እሁድ ጥቅምት 23 ቀን 2012 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ከምርጫ ወረዳ 3፣ 4፣ 5፣ 6 እና 7 አባላት እና ደጋፊዎች ጋር ባደረገው ውይይት ወቅት የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ካቀረቡት ንግግር የተወሰደ ነው፡፡

# የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 19 ለምርጫ ወረዳና ለቀበሌ መዋቅር አመራር አባላት ስልጠና ሰጠ

ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 19 የምርጫ ወረዳው እና የቀበሌ መዋቅር ሥራ አስፈጻሚዎች የፓርቲው ፕሮግራምና በወቅታዊ ጉዳይ ላይ መነሻ ያደረገ ሥልጠና ተሰጠ፡፡ ሥልጠናውን የሠጡት በኢዜማ ጽሕፈት ቤት የፋይናንስ ኃላፊ አዲስ ዳንሳ እና የምርጫ ወረዳ 19 የጥናትና የምርምር ኃላፊ አለማየሁ ንጋት ነበሩ፡፡

የኢዜማ የማደራጀት ተግባርና እንቅስቃሴ በእውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ለማድረግ እና በብቁ አመራር ፓርቲውን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ በአባላቱ መሀከል ጤናማ ፉክክር እና መነቃቃትን ለመፍጠር በማቀድ ሥልጠናው እንደተዘጋጀ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዕለቱ በተዘጋጀው ሥልጠናው ላይ ከ45 በላይ የሚሆኑ የወረዳ እና የቀበሌ አመራሮች ተሳታፊ ሆነውበታል። ከተሳታፊዎችም በመሬት ጉዳይ፣ በሰንደቅ ዓላማ፣ በኢዜማ ትምህርት ፖሊሲ ዙሪያ ጥያቄ ቀርቦ ከመድረኩ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

# ኢዜማ በባሕር ዳር የክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚዎችን እያስመረጠ ነው

ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የምርጫ ወረዳ እና የዞን አደረጃጀቶችን ዘርግቶ አባላትን እየመዘገበ፣ ቢሮዎችንም እየከፈተ ይገኛል፡፡ በባሕር ዳር ምርጫ ወረዳም በስድስት ክፍለ ከተሞች የሥራ አስፈጻሚዎች ማስመረጥ በማስጀመር አራት ክፍለ ከተሞች ላይ ሥራ አስፈጻሚዎችን አስመርጠው መጨረሳቸውን፣ የቀሩትን ሁለት ክፍለ ከተሞች አደረጃጀት የፊታችን ቅዳሜና እሁድ አስመርጠው እንደሚያጠናቅቁ የኢዜማ የባህር ዳር ምርጫ ወረዳ የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ መንግስቱ አማረ አሳውቀዋል፡፡

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት የፓርቲው የማደራጀቱን ሥራ ተዳክሞ እንደነበር የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶክተር) ከአመራሩ ጋር በባህር ዳር ተገኝተው ውይይት ካደረጉ በኃላ የነበሩ ተግዳሮቶች ተፈተው የማደራጀት ሥራ እንደተጀመረ፤ በየወረዳው ቢሮዎችም ለመክፈት እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ ኅብረተሰቡ ለኢዜማ ያለው ምልከታና አተያይ በየጊዜው እየተሻሻለና ጥሩ እየሆነ እንደመጣ እንዲሁም ድጋፍ በማድረግ ላይም እንደሚገኙ፤ በአሁኑ ሰዓትም "ለምን መጣችሁ? ሳይሆን ምነው ጠፋችሁ?" የሚል ብቻ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኪነ ጥበብና በተለያዩ ዝግጅቶች የኢዜማን ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ መመሪያና ደንብ ለማሳወቅ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ በቀጣይም የደም ልገሳ፣ የአካባቢ ፅዳት እንደሚከናወን የውስጥ አደረጃጀቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ሕዝባዊ ውይይት እንደሚዘጋጅ፤ በከተማውም የእግር ጉዞ እንደሚደረግ፣ የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪው አሳወቀዋል፡፡

# ምርጫ ወረዳ 24 ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ አደረጉ

ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ የምርጫ ወረዳ 24 አባላት ጥቅምት ወር ላይ በተነሳው ግጭት ምክንያት በኦሮሚያ ክልል ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች የሚሆን ከ60,000 ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ አደረጉ፡፡

በወረዳ 24 በሴቶች ጉዳይ አስተባባሪነት በወረዳው ከሚገኙ ነዋሪዎችና አባላት የተሰበሰበውን አልባሳት፣ አልሚ ምግቦች፣ የተለያዩ ንፅህና መጠበቂያ እንዲሁም መኮሪኒ፣ ዘይት የመሳሰሉትን ሲሆን የምርጫ ወረዳ 24 አመራሮች በተገኙበት ሀገር ፍቅር ቲያትር በመገኘት የተሰበሰቡትን አልባሳት፣ አልሚ ምግቦች፣ የንፅህና መጠበቂያዎችን ለድጋፍ አሰባሰቢ አስተባባሪ ኮሚቴው አስረክበዋል፡፡

የኢዜማ የምርጫ ወረዳ 24 የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ማርታ ደሳለኝ በምርጫ ወረዳቸው ለሦስት ቀናት ባደረጉት የድጋፍ ማሰባሰብ ከ60,000 ብር በላይ የሚያወጣ ድጋፍ ማግኘት እንደቻሉ፤ በአፋጣኝም መድረስ ስላለበት ላለመዘግየት ሲሉ በአስቸኳይ እንደለገሱ ገልጸው የሰጠነው ድጋፍ ያለ አድሎ ሁሉም ሰው ማኅበራዊ ፍትህ እንዲያገኝ የምንሠራ መሆኑን በደንብ የገለጽንበት ነው ብለዋል፡፡ በቀጣይም ድጋፍ ለሚያሻው ማንኛውም ወገን በመሉ ያለ ልዩነት ኢዜማ ሙሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ አሳውቀዋል፡፡